# ለብርሃኑ ነጋ

*ተኮላ መኮንን*
*ዳካስ ቴክሳስ*
*05/15/2006*

የልጅነት ዘመ ን አንደዋዛ ሳይጫ ወቱበት እያለፈ፤
ሰኞ ማ ክሰኞ ሳይባል አስፋልት ላይ፤ እድሜ እንደ ቀልድ እየከነፈ።
በጊዜው የነበረ የትግል ግዳጅ ወጣ ትነትን እየበላ፤
ለግላጋ ጣቱን ለቃታ ሰጥቶ ፦ ለስላሳ እግሩን በፈንገስ እያቀላ።
«መ ዝሙር ዘፈኑን ተክቶት» ኮረዳ ማየት ቀርቶ፣
ባክስት ባጎት በወንድም ምትክ፦ ጓድ መባል ተተክቶ፣
አባት እናት ተረስተው ፦ቤት ንብረት ባገር ተሞልቴ፤
ትምሕርት ቤት በገባር ጎጆ ፦ ህክምናው በአኩምፓቸር ተቀይሮ፤
በእንጀራ ምትክ በቆሎ ተበልቶ፦ሆድ በበለስ ተወጥሮ።
ለቅንጦት ሲባል ተልባ፦ ለጉዝጓዝ ሲባል ሃምሊ ተበልቶ፣
ካልጋ ወርዶ ካንሶላ ቁራጭ ላይ ተኝቶ፣
ባልጠና ወገብ ዝናር ታጥቆ፦ በልጅነት ጫንቃ ብረት አንግቶ።
ገና ከትግሉ ሲቀላቀል መስዋእትነቱን ተቀብ ሎ፣
ኑዛዜውን ለጓዶቹ ትግሉን ቀጥሉ ብቻ ብሎ ።
አገር ለራስ ቅንጦ ት ሳይሆን፦ ለሕዝብ እኩልነት መ ሆኑን አምኖ፤
ላብ አደሩን ነፃ ሊያወጣ ከአፈር ገፊው እኩል አፈር ዘግኖ፤
ከቤት ከቀየው እርቆ በዱር በገደል ፈንኖ።
ለዓላማ መሞት ክብር እንደሆነ ያመነ፦ እህት ወንድሙን ለትግሉ የገበረ፣
ካላመነበት የሚናገር፦ የተሰለፈበት ድርጅት ሲዛነፍ እንኳን፦
አንገቱን ያልሰበረ፣
ትግል ብሎ ህይወቱን እንዳልገፋ በትግሉ እንዳላደገ፤ ዛሬ ዘብ ጥያ ተወረወረ????
ሲሆን ምስጋና ምርቃት እውቅና ይገባው ነበረ።
ወጣቱ ታጋይ ብርሃኑ ነጋ እግሩ በእግረ ሙቅ ታሰረ፣
እጁ በፊሮ አበጠ ዓይኑ በጨለማ  ታወረ።

እኔ እንደትላንቱ «ጓድ »አይደለሁ  አቋምህን አልገመግም ፥
ካጠገብህ አልተሰለፍኩ ብሩሕ ጨረር ዛሬ አላልም ።
እኔ እንዳንተ «ልብ ም »የለኝ ሁሉን ነገር ትቼዋለሁ ፣
ታገሉ ብየም አልሰብክ ዳግም በስደት ተወጥሬአለሁ ፣
በግለኝነት ተሳስሬ በሕይወት እጣ ወድቄአለሁ፣
ያም ቢባል የቆረጡ ትን ግን አደንቃለሁ፣
ለክቡር ሥራቸው ም እሰግዳለሁ፣
ብርሃኑ ምንም ባቋምህ ባልስማማ ቆራጥንትህን ግን አወድሳለሁ ።

ዝም በል ወንድሜ
ትላንት ወንጀል የነበር ፥ዛሬ ገድል ሆኖ አይተናል፣
«አንጃ» ብ ለን ዛሬ አንጠራህ፦ ተጋዳይ መ ሆንክን አም ነናል፣
በገንዘብ አልታለልክ፦ ኖሮህም ስትፋለም አስተው ለናል።
ድሮስ መች ታማ ህ በድህነት፦ በወጣ ትነትህ እንጂ፣
ጌዶችህን ጠ ላት ሳይሆን ሲያስተኛቸው የወገን ፈንጂ፤
ድሮስ መች ታሰርክ በሙ ስና፥ ተናገረ ተቃወመ ብ ለው ፣
ድከመ ታቸው ን አወላግደው ፥ አላማ ቸው ን ደበላልቀው ፣
ነፍጠኛ አይሉህ ነገር ዛሬ፥ የትላንቶቹም አልቀናቸው ፣
እዉ ነት እየፈካ እንደመ ጣ እነዚህንም አይለቃቸው ፣
ተዋግተህ ጦርነት ያከትም ደም ማ ፍሰስ ይብቃ ባልካቸው ፣
ከትግራይ አባረው ህ መ ርካቶ ብ ትጠ ብቃቸው ፣
የመ ብ ት ነገር ብታነሳ በኩልነት ብትገጥማ ቸው ፣
ዲሞክራሲው ተረሳና እስራት ሆነ ምላሻቸው፣
አባይ ኢ ትዮጵያ ያሉበት እሬት ሆነ ምላሳቸው ፣
ሕ ዝ ብ ሆነ ፈራጁ ም ርጫ ሆነ ጠ ላታቸው ።
ብ ርሃኑ የትላንት ወጣ ት ብ ርሃኑ ያሁንም ታጋይ፣
በርታ እንጂ፲ አንሞት እኛ፦ መፈታትህን ገና ሳናይ።

አንሞት አንሞት አንሞት

አትሞት ያመንከበትን ፈጽመህ ሕልምህን እውን ሳታደግ፤
አምልጠህ የለ ከድርጅት ግርፊያ እስራት እንኳን ከዚህ ከትላንቱ ፋሽስት ደርግ።

አትሞት እኛም አንሞት